# የወንጌል መሰበክ



ጌታ ኢየሱስ የዳግም ምጽዓቱን ምልክት ከነገራቸው በኋላ የነገራቸው ሁሉ ገና "የምጥ ጣር" እንደሆነ ገለጻላቸው። ይህ ማለት መጨረሻው ሲመጣ ደግሞ እጅግ የከፋ ዘመን እንዳለ የሚያመለክት ነው። "ለአሕዛብም ሁሉ ምስክር "እንዲሆን ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል፥ በዚያን ጊዜም መጨረሻው ይመጣል።" *(ማቴ.24:14)* ከ1990 ጀምሮ እስካሁን ለ4ቢሊዮን ለሚሆኑ ሰዎች ወንጌል ተሰብኮላቸዋል። ከዚህም የተነሳ በ251 አገሮች የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ተተክላለች። በየአመቱ 4 ቢሊዮን የወንጌል በራሪ ወረቀቶችና 120 ሚሊዮን መጽሐፍ ቅዱሶች በአለም ዙሪያ ይበተናሉ።

ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ ወይንም በከፊል በአሁን ሰዓት በ2ሺ 62 ቋንቋዎች ተተርጉሟል። ከዚህም የተነሳ 98 ከመቶ የሚሆነው የምድር ህዝብ ወንጌልን የመስማት እድል አግኝቷል። ወንጌል ከ2,000 በላይ በሚሆኑ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ጣቢያዎች ለአለም ህዝብ እየተሰበከ ነው። በታሪክ ውስጥ አሁን እንዳለንበት ዘመን ወንጌል ለፍጥረት ሁሉ ተሰብኮ አያውቅም። እያንዳንዱ ህዝብና ነገድ ኢየሱስ ክርስቶስ ተሰብኮለታል። ይህ ማለት ሁሉም ተቀብለው ማለት አይደለም...ነገር ግን አልሰማንም ነበር የሚል ማንም አይኖርም ማለት ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም እንደተናገረው እውነትም ወንጌል ለፍጥረት ሁሉ እየተሰበከ ነው! የወንጌል በፈጠነና በተንሰራፋ መንገድ መሰበኩ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት ምልክት ነው።